መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 42928

ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ አክሊሉ አበባው - ቀረቡ።

**ተጠሪ፡-** ድራጋዶስ ኮንስትራክሽን - የቀረበ የለም።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም. በመሠረተው ክስ መነሻ ነው። የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ አካባቢ የመንገድ ሥራ ሲያከናውን በአመልካች ንብረት ላይ ግምቱ ብር 25,569.85 /ሃያ አምስት ሺህ አምስት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ አምስት ሳንቲም/ የሆነ ጉዳት ማድረሱን ገልፆ ይህንኑ ገንዘብ ከነወለዱ ወጪው ጋር እንዲተካ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው። የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተከሣሽ ድርጅት በግሪክ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመ አድራሻውም አቴንስ የሆነ የውጭ ሀገር ኩባንያ ነው፣ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥም አልተመዘገበም ስለዚህ በመልካችና በተጠሪ መካከል የሚነሳ አለመግባባት በየትኛው ሀገር ሕግ ይታያል፣ በየትኛው ፍርድ ቤት ይታያል የሚል የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ስለሚያስነሳ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስቶ ተከራክሯል። ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ይህንኑ የተጠሪን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ጉደዩን መርምሮ ጉዳዩ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ የሚያስነሳ በመሆኑና ሥልጣኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም ሲል የአመልካችን ክስ በብይን ዘግቷል። በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

አቅርቦ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በተጠሪና በአመልካች መካከል ያለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ጉዳቱ የደረሰው ተጠሪ ኢትዮጵያ ውስጥ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት ስለሆነ እና በንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት ደግሞ ክሱ መመስረት ያለበት ጉዳቱ በደረሰበት ሀገር ሕግና ፍርድ ቤት መሆኑ እየታወቀ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2ሀ/ ያላግባብ ተጠቅሶ ክሱ መዘጋቱ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን መዝጋቱ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ጉዳዩ በቃል ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይንና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ክስ መሠረት ያደረገው ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከት የሚገዙ ድንጋጌዎች መሆኑ፣ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ጉዳት ያደረሰው ስራውን በኢትዮጵያ ውስጥ ሲያከናውን መሆኑን ክሱ የቀረበውም ጉዳቱ በደረሰበትና ንብረቱ በሚገኝበት ክልል በሚገኘው ፍርድ ቤት መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር የንብረት ጉዳት ካሣ በመሆኑ ክሱ ሊመሠረት የሚገባው የገንዘቡ መጠን ግንዛቤ ውስጥ ሲገባ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ የሚወስነው የሥረ- ነገር ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ጉዳቱ በደረሰበትና ንብረቱ በሚገኝበት ክልል በሚገኘው ፍርድ ቤት ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 27/1/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ አንፃር ተገንዝቦ አይቶ የመወሰን ስልጣን የራሱ ሆኖ እያለ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2/ሀ/ ድንጋጌን ያለቦታው ጠቅሶ የአመልካችን ክስ መዝጋቱ እና ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይህንኑ መቀበሉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## **ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09737 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69916 ሕዳር 15 ቀን 2001 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው በመሆኑ የአመልካችን ክስ ተቀብሎ ግራ ቀኙን በቀሪ መከራከሪያ ነጥቦች ላይ በማከራከር ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ